የኢትዮጵያ ዘውድ ምክር ቤት

THE CROWN COUNCIL OF ETHIOPIA

HIS IMPERIAL HIGHNESS PRINCE ERMIAS SAHLE-SELASSIE HAILE-SELASSIE
PRESIDENT

# የኢትዮጵያን ሕብረት ያረጋገጠው የተስፋ መብራት ከተቀጣጠለ ከ125 ዓመታት በኋላ

*ከኢትዮጵያ ዘውድ ምክርቤት ፕሬዘዳንት ከልዑልነታቸው ልዑል ኤርሚያስ ሣህለ ሥላሴ ኃይለ ሥላሴ የተሰጠ መግለጫ*

*የ125 ተኛውን የአድዋ ድል በተመለከተ*

ዓጼ ምኒልክ ሃገሪቷን የወረረውን ጠላት ለመመከት የአንድነት ጥሪ በማድረግ የኢትዮጵያን ሕዝብ የሰበሰቡበት ወቅት 125 ዓመታት ሆኖታል፡፡

ከሁሉም የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት ግዛቶች በተሰባሰቡት ኢትዮጵያውያን ሕብረት፤ በየካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም የተገኘው የአድዋ ድል፤ ለሀገሪቱ የነጻነት ጮራ ያንጸባረቀና ክብርን ያጎናጸፈ ሲሆን፤ የአፍሪካ ህዝቦችን ያነሳሳና መላውም ዓለም ለኢትዮጵያ አክብሮትን የሰጠበት ወቅት ነው፡፡

የአድዋ ድል የሚያረጋግጠው፤ የራሳቸውን ሕይወት ለውድ ሀገራቸው ለመስጠት የተዘጋጁ፤ ከተለያዩ የሀገሪቷ ንጉሠ-ነገሥት ግዛቶች የተሰባሰቡ ሀገር ወዳዶች፤ የሀገራቸውን ነጻነትና ድንበር ላለማስደፈርና የወደፊት የኑሮ እጣቸውን በራሳቸው እጅ ለማድረግ ወስነው ይህን ክቡር ዓላማ ተግባሪዊ ማድረጋቸውን ነው፡፡ አድዋ፤ በኢትዮጵያውያን መካካል ጥቃቅን ልዩነቶች የቀሩበትና የእያንዳንዱ ሰው ችሎታና የትግል ድርሻ የተከበረበት ወቅት ነበር፡፡ አድዋ፤ እኛ ኢትዮጵያውያን፤ በአንድ ላይ ስንተባበር፤ ለማድረግ የሚያቅተን ነገር አለመኖሩን ያየንበት ግዜ ነበር፡፡ አድዋ፤ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሌላውን ኢትዮጵያዊ ያከበረበት ወቅት ነበር፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥትም ይህን ታሪካዊ ክስተት መደበኛ በዓል ሆኖ በዚህ ዓመት በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲከበር በመፍቀዱና በማክበሩ ደስታችንን መግለጽ እንወዳለን፡፡

የዘውዱ ምክርቤት በዚህ ዓመት የኮቪድ-19 በሽታ ባስከተለው የጉዞ እገታ ምክንያት የአድዋን ድል ባያከብረውም፤ ከዚህ ቀን ጀምሮ ለአንድ ዓመት ያህል ማለትም እስከ የካቲት 22 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ ይህን በዓል ሲያስብ ይቆያል፡፡ በሚቀጥለው ዓመትም ከዚህ በፊት በመደበኛነት ሲያደርገው እንደነበረው፤ ይህን የኢትዮጵያን ህዝቦች ሕብረት አረጋጋጭ የሆነውን የአድዋ በዓል በሚገባ ለማክበር ዝግጁ ነው፡፡

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ፡፡ እግዚአብሔር የዓጼ ምኒልክንና የዓጼ ኃይለ ሥላሴን ትዝታ ሕያው ያድርግ፡፡